


## የCAMBRIDGE ከተማ አስተዳደር

# ዜሮ የጋዝ ልቀት የትራንስፖርት ዕቅድ

**2025** | የተተረጎመ ማጠቃለያ

# ዋና ዋና ማጠቃለያዎች

## ለምን ዜሮ የጋዝ ልቀት ትራንስፖርት ዕቅድ አስፈለገ፣ እና ለምን አሁን?[1]

የአየር ንብረት ቀውስ በከፍተኛ ሙቀት፣ በአየር መበከል እና በአስከፊ የአየር ንብረት ክስተቶች አማካኝነት በCambridge ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል። የከተማው አስተዳደር እስከ 2050 ዓ.ም ድረስ የተጣራ ዜሮ የግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ልቀት ላይ ለመድረስ ቃል የገባ ሲሆን፣ የተጣራ ዜሮ የጋዝ ልቀት[2] የሚለው ቃል የሚመረተው የግሪንሃውስ ጋዝ መጠን እና ከከባቢ አየር ውስጥ የሚወገደው መጠን እኩል የሚሆንበትን ሚዛን ያመለክታል። ትራንስፖርት የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቶች ዋና ምንጭ ሲሆን፣ 94% የሚሆነው የከተማዋ ልቀት ከግል የመንገድ ተሽከርካሪዎች ይመነጫል።[3] ዜሮ የጋዝ ልቀት ትራንስፖርት ዕቅድ (ZETP) ዓላማው ይበልጥ ተደራሽ እና ፍትሃዊ የትራንስፖርት ስርዓት በመገንባት እነዚህን የአየር ብክለት ልቀቶች ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሲሆን፣ በተለይም ነዋሪዎች ለውጦችን በሚረዱበት እና በሚላመዱበት ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ የቀድሞ የዕቅድ አወጣጥ ኢፍትሃዊነቶችን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል።

**ይህ ዜሮ የጋዝ ልቀት ትራንስፖርት ዕቅድ በአራት ዋና ዋና ግቦች ላይ የተመሠረተ ነው፦**

1. ከትራንስፖርት አገልግሎት የሚመነጭን የአየር ንብረት ብክለትን ማስወገድ
2. በCambridge ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ይበልጥ ተደራሽ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና አስደሳች ማድረግ
3. የኢኮኖሚ ዕድሎችን ማሻሻል እና ቀደም ሲል የነበሩ ኢፍትሃዊ አሰራሮችን ማስተካከል
4. ይበልጥ ጠንካራ እና እርስ በርስ የተሳሰረ ማህበረሰብ መገንባት

## ዕቅዱን እንዴት አዘጋጀነው

ዜሮ የጋዝ ልቀት ትራንስፖርት ዕቅድ የተዘጋጀው ሰፊ ተሳትፎን በሚያረጋግጥ መንገድ በመሆኑ፣ በተለይ ድምፃቸው ለማይሰማ፣ አገልግሎት ለተጓደለባቸው እና ቀደም ሲል ለተገለሉ ወገኖች ቅድሚያ በመስጠት የተለያዩ አስተያየቶችን ለማካተት ተችሏል። ዓላማው መተማመንን መፍጠር፣ ትስስርን ማጠናከር እና ቀጣይነት ያላቸውን የተሳትፎ ጥረቶች መደገፍ ነበር።

ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ለመቅረጽ እና ለማዳበር ከአማካሪ ቡድን፣ ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴዎች እና ከመላው ማህበረሰብ ጋር በጋራ ሰርተናል። ከ50 በላይ ከሆኑ የሕዝብ መድረኮች፣ የትኩረት ቡድን ውይይቶች እና ስብሰባዎች የተገኙ አስተያየቶችን ያካተተው ይህ ሂደት፣ ሊወሰዱ የታሰቡ እርምጃዎች እንዴት እንደሚሻሻሉና የትኞቹ ሐሳቦች ተቀባይነት አግኝተው እንደሚካተቱ ወይም እንደሚቀነሱ ለመወሰን ረድቷል።

የከተማዋ የሥራ ኃላፊዎች በCambridge ውስጥ ያለውን የትራንስፖርት ልቀት ለመገመትና ሊወሰዱ የታሰቡ እርምጃዎች የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመተንበይ ከአማካሪዎች ጋር በጋራ ሰርተዋል። ይህ የመነሻ መረጃ እስከ 2050 ዓ.ም ድረስ መቀነስ ያለበትን የልቀት መጠን ለመወሰን እና የታቀዱ እርምጃዎች ለእነዚያ ቅነሳዎች እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ለመገምገም ጥቅም ላይ ውሏል።

## ከማህበረሰብ አባላት የተማርነው

- ሰዎች የጉዞ ዘይቤያቸውን ለመቀየር ዝግጁ ቢሆኑም ለውጡን ተግባራዊ ለማድረግ ግን እገዛ ይፈልጋሉ።
- ሰዎች ድምፃቸው እንዲሰማ የሚፈልጉ ሲሆን በጉዳዩ ላይም ተግባራዊ እርምጃ ሲወሰድ ማየት ይሻሉ።
- የመኪና ባለቤት መሆን ወይም ማቆሚያ ማግኘት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ ኢፍትሃዊነት ሊመስል የሚችል ሲሆን፣ ይህም በራሱ የማህበረሰቡን እኩል ተጠቃሚነት የሚጎዳ ሆኖ ሊታይ ይችላል።

- የሚከናወኑ ለውጦችን በተመለከተ ግልጽ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ እና ግንኙነትን ማጠናከር ያስፈልጋል።
- ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች ተገቢውን ክብር የሚሰጡ እንዲሁም ምቹና እምነት የሚጣልባቸው አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ማቅረብ ያስፈልጋል።
- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች (EVs) የመፍትሄው አንድ አካል ብቻ ናቸው።
- እያንዳንዱ ፍላጎት የራሱ የሆነ መፍትሔ የሚሻ በመሆኑ፣ ሰፊ የሆኑ አማራጮችን ማዘጋጀት ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

## በዕቅዱ ውስጥ ምን ተካቷል?

ዕቅዱ በስድስት ዘርፎች የተከፋፈሉ ተግባራትን እና ምክረ ሐሳቦችን የያዘ ሲሆን፣ ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፦

1. **የማህበረሰብ ተሳትፎ፦** የሰዎችን የትራንስፖርት ተሞክሮ ለማሻሻል ማህበረሰቡን በእኩልነትና በፍትሃዊነት ማሳተፍ
2. **አውቶብሶች እና ሽትሎች፦** የአውቶብስ እና የሽትል አገልግሎትን ማሻሻል
3. **ብስክሌት፣ በእግር መጓዝ እና ማይክሮሞቢሊቲ፦** ሰዎች በእግር፣ በብስክሌት እና በስኩተር እንዲጓዙ ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስደሳች ሁኔታዎችን መፍጠር
4. **የመኪና ጉዞዎችን መቀነስ፦** የመኪና ጉዞ አስፈላጊነትን ለመቀነስ ለሰዎች ሰፊ የጉዞ አማራጮችን ማቅረብ
5. **የመኪና ባለቤትነትን መቀነስ፦** የመኪና ባለቤት አለመሆንን ቀላልና ምቹ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን መፍጠር
6. **የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች፦** ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የሚደረገውን ሽግግር ማበረታታት

የከተማው አስተዳደር ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተፅዕኖ፣ አፈጻጸም፣ ወጪ እና ከማህበረሰቡ የተገኘን አስተያየት መሠረት በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት ቅድሚያ ሰጥቷል።

እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ነዋሪዎች የትራንስፖርት አማራጮችን እና ቅናሾችን እንዲያገኙ ማገዝ
- በዋና ዋና መንገዶች ላይ የአውቶብሶችን ፍጥነት እና አስተማማኝነት ማሻሻል
- ብስክሌት እና የBluebikes አገልግሎትን ለብዙሃኑ ተደራሽ ማድረግ
- የህዝብ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ (EV) እና ማይክሮሞቢሊቲ ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎችን ማስፋፋት

## ቀጣዩ እርምጃ ምንድን ነው?

የCambridge ቀጣዩ እርምጃ በ2026 ዓ.ም የሚጀመረውንና የከተማ አቀፍ የትራንስፖርት ዕቅድ ሂደት የሆነውን የCambridge ተደራሽነት እና ምቹ እንቅስቃሴ ዕቅድን ማዘጋጀት ይሆናል። ይህ ዕቅድ በZETP መሠረተ ሐሳብ ላይ የሚገነባ ሲሆን፣ አሁን ያለውንና የወደፊቱን የCambridge ነዋሪዎች ፍላጎት የሚያሟላ የትራንስፖርት ሥርዓት ለመፍጠር እንዲቻል የመሬት አጠቃቀምን፣ ደህንነትን፣ ተደራሽነትን እና ዘላቂነትን ይበልጥ ያቀናጃል።

# ማስታወሻዎች

1 የCambridge «Zero Emissions Transportation Plan» (ዜሮ የጋዝ ልቀት ትራንስፖርት ዕቅድ) በመዘጋጀት ላይ በነበረበት ወቅት መጀመሪያ «Net Zero Transportation Plan» (የተጣራ ዜሮ የጋዝ ልቀት ትራንስፖርት ዕቅድ) ተብሎ ይጠራ ነበር። የማህበረሰቡ አባላት «Net Zero» (የተጣራ ዜሮ የጋዝ ልቀት) ከሚለው ቃል ይልቅ ይበልጥ ግልጽ የሆነ መጠሪያ እንዲኖር በመጠየቃቸው ምክንያት የዕቅዱ አዘጋጆች ስሙን ሊቀይሩት ችለዋል።

2 «የተጣራ ዜሮ የጋዝ ልቀት» ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት https://www.nationalgrid.com/stories/energy-explained/what-is-net-zeroን ይጎብኙ።

3 በ2019 ዓ.ም የወጣው Cambridge Community GHG Inventory (የCambridge ማህበረሰብ የግሪንሃውስ ጋዝ ዝርዝር መዝገብ) ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ገጽ 27ን ይመልከቱ፡- https://www.cambridgema.gov/-/media/Files/CDD/Climate/ghginventory/2019cambridgecommunitywideghginventory_summaryreport.pdf


TOW ZONE
NO STOPPING ANYTIME
BLUEbikes